ሚያዝያ 2011 ዓ. ም

## የወቅቱ የኢትዮጵያ ሁኔታና የኢሕአፓ የመፍትሄ ሃሳቦች

የሰው ልጆች ሁሉ በሰውነታቸው አንድ ቢሆኑም፣ በመውለድና በመዋለድ የተነሳ በመባዛታቸው የእኔ የሚሉት የየራሳቸው ማንነት መፍጠር ከጀመሩ ዘመናት ተቆጥረዋል። ግንኙነት ለሰው ልጆች ቁልፍ የሆነ አብሮ የመኖር መንገድ ስለሆነ ቋንቋ እጅግ ወሳኝ ከሆኑትና በቡድኖች መካከል የማንነት ልዩነት ከሚፈጥሩት ነገሮች አንዱ ነው። የማንነት ጥያቄም በሰዎች መካከል መኖሩም በዚህ ጊዜ ያበቃል የሚባል ጉዳይ አይደለም። የዘር ማንነት በፖለቲካና በሌሎች ምክንያቶች ሊቀየር እንደሚችልም ከታሪክ ማየት ይቻላል። በመሆኑም ብሄርተኝነት አይቀሬ የዘመናዊነት ውጤት መሆኑን መቀበል የግድ ይሆናል። በዓለም ታሪክ ውስጥ ብሄርተኛነት የተጀመረው በአውሮፓ መሆኑ ሲነገር እንደ አውሮፓም በብሄረተኛነት ሳቢያ ብዙ ሕዝብ ያለቀበት የዓለም ክፍል አለመኖሩም ይታውቃል። ብሄረተኛነት በዘመናዊ መልኩ ወደ ሦስተኛው ዓለም የገባው በሃያኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን በብሄረተኛነት ምክንያት በተቀሰቀሱ ጦርነቶች አንድ መቶ ሚሊዮን ያህል የዓለም ሕዝብ ሕይወቱን ማጣቱም ተዘግቧል። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሂትለርና ሙሶሊኒ በሕዝብ ማንነት ላይ ያጠነጠነ አክራሪ ብሄረተኛነትን በማነሳሳት፣ ከ60 ሚሊዮን በላይ ለሆነ የአውሮፓ ሕዝብ እልቂትና ለአውሮፓ መፈራረስ ምክንያት ሆነዋል። በኢትዮጵያም ለዓመታት በተካሄዱ የብሄርተኛ ጦርነቶች ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ ማለቁ ማጣቀሻ የሚያስፈልገው ጉዳይ አይደለም።

የብሄርተኝነት ፖለቲካ አቀንቃኞች በአንድ ሕዝብ ባህል ወይም ቋንቋና ሃይማኖት፣ በአጠቃላይ በማንነቱ ላይ በመመሥረት ለዚያ ሕዝብ የኤኮኖሚ ጥቅሞች፣ የባህልና የፓለቲካ መብቶች…ወዘተ በማስገኘት ሰበብ በዙሪያቸው በማሰለፍ ሥልጣን ላይ ለመውጫነት ሊገለገሉበት ሲታትሩ ይታያሉ። በዚህ ብቻ አያበቃም፣ የአክራሪ ብሄረተኛ አስተሳሰብ የሌሎችን ታሪክና ማንነት በማጥፋት የራሱን ተወላጆች የጥቅም የበላይነት የሚያረጋግጥበትን መንገድ መተግበርም ይፈልጋል። ኢትዮጵያም ውስጥ ላለፉት ሦስት አሥርተ-ዓመታት አካባቢ የተካሄደው ይኼው ነው። ሀገሪቱን በቋንቋ በመከፋፈል የጎሣ

ጥላቻ ሲሰበክባት ባጀ፤ እነሆ እንክርዳድ የዘራ የስንዴ ምርት አይጠብቅምና ዛሬ የዘሩልንን ማጨድ ግድ ሆነብን።

ኢትዮጵያ በሕዝቦቿ መካከል ጎሣና ሃይማኖት ለዘመናት የመለያየት ምክንያቶች ሳይሆኑ፣ በሰላም፣ በፍቅር ብሎም በአብሮነት የተኖረባት አገር ነች። በዚህም የተነሳ በአብዛኛው፣ አንድ ዜጋ የኔ ብሄር ከዚህ ብቻ ነው ብሎ ሊናገርበት የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩን መናገር ከእውነት የራቀ አይደለም። እንዲህ ስለሆነም ነው የግዛት አንድነቷን አስከብራና የሕዝቧን ሉዓላዊነት አስጠብቃ እዚህ የደረሰችው። ይህ ሲባል ግን የሥርዓት ጭቆናና በደል አልነበረም ማለት አይደለም። በደል በመኖሩ ምክንያት የመብት ተሟጋቾችና የፖለቲካ ድርጅቶች ለእኩልነትና ለዴሞክራሲ ሲታገሉ ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለዋል።
ላለፉት ሦስት አሥርተ-ዓመታት የሕዝቧንና የሃገሪቷን ታሪክ በማዛባት፣ በወንድማማችነትና በሰላም አብሮ የኖረን ሕዝብ በማናቆር እርስ በርሱ በጠላትነት እንዲተያይ ያደረገ ጎሰኛ ቡድን ሥልጣን በመያዝ የሕዝቡን ሰላም እያወከ የአገሪቱን ሕልውና አስጊ ደረጃ ላይ አድርሷል። ይህን የጠባብ ብሄርተኝነት አካሄድ ወደ ከፋ ደረጃ በማድረስ ባለማሰለስ ያደረጉት የጥላቻ ቅስቀሳ ለዘመናት አብሮ የኖረን ሕዝብ በነፍጥ ሳይቀር እንዲገዳደል አደረጉት። በዚህ አካሄድ የሕዝቡን ግንኙነት ወደ "እኛ" እና "እነሱ" አመለካከት እንዲወርድ በማድረግ ለዘመናት ከኖረበት፣ እትብቱ ከተቀበረበት፣ ሀብት ንብረት ካፈራበት አካባቢ እያፈናቀሉ በገዛ ሀገሩ ውስጥ ስደተኛ እያደረጉት ነው። ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ የተፈናቀለው ወገናችን ቁጥር ወደ ሦስት ሚሊዮን እንደሚጠጋ ተዘግቧል።
በዶ/ር አብይ በሚመራው የለውጥ አራማጅ መንግሥት በተደረገ ጥሪ፣ በውጭ አገር ያሉና ነፍጥ አንስተው የመሣሪያ ትግል እናደርጋለን ያሉ ድርጅቶች በሀገራቸው ውስጥ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ሀገራቸው ከገቡ ኃይሎች ውስጥ አንዳንዶቹ በማፈናቀሉ ሂደት ዋና ተዋንያን መሆናቸው አሳዛኝ ሁኔታን ፈጥሯል። በዚህ መልክ የገቡ ኃይሎች ነፍጥ አንስተው ሰላማዊውን ሕዝብ ማጥቃትና ማፈናቀል ተግባር ላይ ሲሰማሩ፣ በሰላማዊ መንገድ መታገል አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ሌላው አሳሳቢው ጉዳይ ደግሞ በማፈናቀል ሂደቱ ውስጥ፣ እጅግ በማይጠበቅ ሁኔታ፣ ሕዝቡን ሊከላከሉለት የሚገባቸው የመንግሥት አካላት ትዕዛዝ አልተሰጠነም በማለት ተጠቂውን ወገናችንን ለማዳን አለመቻላቸው ወይም አለመፈለግ ነው።

የሽግግር ጊዜ አልጋ በአልጋ እንደማይሆን የሚታወቅ ቢሆንም በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ሞት፣ ስቃይና እንግልት ግን ዋንጫው ሞልቶ እየፈሰሰ ነው። በዚህ አጭር የለውጥ ሂደት ወቅት የደረሱትን ጥቂት አሰቃቂ ክስተቶች ለመጥቀስ ያህል፡

- በሶማሌና በኦሮሞ ሕዝብ መካከል የተከሰተ የግድያና የማፈናቀል ሁኔታ፣
- በሻሸመኔ አካባቢ ከሰብዓነትና ከኢትዮጵያዊ ባህል ውጭ በተካሄደው የቡድን ፍርድ ሰው ዘቅዝቆ መስቀል፣
- በጌዴዎና በኦሮሞ ሕዝብ መካከል በተክሰተ ማንነትን መሠረት ያደረገ ችግር የደረሰው የሰው ልጅ ስቃይ፣ በተለይም የሕፃናት ሰቆቃ፣
- በቤኒሻንጉልና አማራ ሕዝብ መካከል የተፈጸመው ግድያና ማፈናቀል፣
- በአማራ ክልል በምዕራብ ጎንደር የተፈጸመው ግድያና መፈናቀል፣
- በአዲስ አበባ ዙሪያ፣
    - በቡራዩ አካባቢ የተካሄደው አስደንጋጭ ማንነትን የተከተለ ጭፍጨፋና ማፈናቀል፣
    - በለገጣፎና አጃምባ ሠፈር የተካሄዱት መኖሪያ ቤቶችን ማፍረስና ማፈናቀል፣
    - በሱሉልታ ተፈጥሮ የነበረው የነዋሪዎቹን ሰላም ያወከው የቤት ማፍረስ ማስፍራሪያ፣
    - በአዲስ አበባ የይገባኛል ጥያቄ ላይ መሠረት ያደረገው የጋራ የመኖሪያ ቤቶችን ዕጣ አስመልክቶ የተከሰተው ከሰላማዊ ትግል እሳቤ እጅጉን የራቀ እንቅስቃሴ፣
- አሁን ደግሞ በወሎና በሰሜን ሸዋ በተደራጀና በታጠቀ ኃይል የተካሄደው ግድያና ቤተ ክርስቲያናትን የማቃጠል አስደንጋጭ ዘመቻ ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ቀደም ሲል ለተፈጸሙት አሰቃቂ ወንጀሎች መንግሥት የሕግ የበላይነት ማረጋገጡን ባለማሳየቱ፣ ሕዝቡ በለውጡ ሂደት የሰነቀው ተስፋ ከጊዜ ወደ ጊዜ አጠራጣሪ እየሆነ እንዲሄድ አድርጎታል። በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የመንግሥትን ጥርት ያለ አቋም ማወቅ አስቸጋሪ የሆነባቸው ጉዳዮች የመኖራቸውን ያህል፣ በለውጡ ተጎድተናል የሚሉ ኃይላት በሚሠሩት ደባ ሕዝብንና መንግሥትን እየጎዱ ለመሆናቸው አጠያያቂ አይደለም። ሰሞኑን ከወሎ እስከ ሰሜን ሸዋ እየደረሰ ያለው በማንነት ላይ ያነጣጠረና ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን የጣሰ እንቅስቃሴ በአማራው ሕዝብ ላይ ያደረሰው ጉዳት እጅግ ከፍ ያለ ትኩረትን የሚሻና አፋጣኝ እርምጃ የሚጠይቅ ነው። ከከሚሲ የጀመረውና

በሰሜን ሸዋ ዞን በሚገኙት በካራቆሬ፣ በአጣዬና በማጀቴ የቀጠለው በሰላማዊ ነዋሪዎች ላይ የተፈጸመው ኢ-ሰብዓዊና ዘግናኝ ድርጊት ህሊና ላለው ሁሉ አሳዛኝ ነው። ሕይወት ጠፍቷል፣ ብዙዎች አካለ ጎዶሎ ተደርገዋል፣ ንብረታቸው ተዘርፏል፣ ተቃጥሏል፣ ቀሪውም በስጋት ይጠብቃል፤ ወጥቶ መግባት ብርቅ ሆኗል። የጥፋት ኃይሎች መሪዎች በሀገሩ የሚኖረውን የተዛመደና ለረዥም ጊዜ አብሮ የኖረውን ሕዝብ በማያውቀውና ባላሰበው ነገር እየጎተጎቱ ለዚህ እንዳደረሱት አሌ የሚባል አይደለም።

በምንም መስፈርት ቢለካ፣ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተፈጸመ ያለው ድርጊት ከፍተኛ ወንጀል ለመሆኑ አጠያያቂ አይሆንም። ወንጀል በተደጋጋሚ ሲፈጸም ደግሞ የሕግ የበላይነት ያልሰፈነበት ሥርዓት ላይ እንዳለን የሚያሳይ ነው። የመንግሥት አንዱና ዋነኛው ተግባር ሕዝቡ ያለስጋት በሰላም እንዲኖር፣ መሠረታዊ ዴሞክራሲያዊና የሰብዓዊ መብቶቹ እንዲከበሩ ማድረግ ነው። ይህ እየተፈጸመ ባለመሆኑ መንግሥት ዋነኛ ኃላፊነቱን አልተወጣም ማለትን ያስከትላል። መንግሥት ይህን እኩይ ተግባር በሚፈጽሙ አካላት ላይ የሕግ የበላይነትን በማስከበር የወሰደው እርምጃ እጅግ ደካማ ነው። ሕዝብ ሲሞትና ሲሰቃይ እየታየ በጥናት ላይ የተመሠረተ እርምጃ ለመውሰድ በዕቅድ ላይ መሆንን መግለጽ መንግሥት የሕዝብን ደህንነት ለማስጠበቅ ያለውን ዝግጁነት ከጥያቄ ውስጥ ያስገባል። ወንጀል እየፈጸሙ ያሉ ኃይሎች ወታደራዊ ሥልጠናዎች እየወሰዱ እንደሆነ ሕዝብ ጥቆማ እያደረገ የመንግሥት አካላት በቸልታ ማለፋቸው፣ የታጠቀ ኃይል ተራራ ላይ መሽጎ በሕዝብ ላይ ሲተኩስ እየታየና በሕዝቡ ላይ ጥቃት ከደረሰ በኋላም አፋጣኝ እርምጃ አለመወሰዱ በማሳያነት ይጠቀሳል። በሕዝቡ ላይ የጭካኔ እርምጃ የሚወስዱ፣ ሰላም የመንሳትና የማፈናቀል ተግባር የሚፈጽሙ ኃይሎች ምንም ሆኑ ምን ወንጀለኞች በመሆናቸው በአስቸኳይ በሕግ ሊጠየቁ ይገባል።

ኢሕአፓ በወገኖቻችን ላይ የተፈጸሙትን እኩይ ተግባሮች አጥብቆ ይቃወማል። በከሚሴ በአጣዬ በማጀቴና በሌሎችም ቦታዎች አረመኔያዊ ተግባር የፈጸሙ፣ የእምነት ተቋማትን ያቃጠሉ፣ መንገድ ዘግተው ነፍሰጡሮችንና በጠና የታመሙ ህሙማንን ለሞት የዳረጉ፣ ግለሰቦችና ቡድኖች ለጥፋታቸው ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲሰጣቸው ይጠይቃል። በተጨማሪም ኑሮን ለማሸነፍ ሲኳትኑ ውለው ከደሳሳ ጎጇቸው ገብተው ማረፍ ላልቻሉ፣ በዘረኝነት የጥላቻ ፖለቲካ መዘዝ በደረሰባቸው ጥቃት ሕይወታቸውን ላጡ ወገኖች ኃዘኔታውን፣ በስቃይና በእንግልት ውስጥ ላሉ ወገኖች ደግሞ ወገናዊነቱን ይገልፃል። እነዚህ ወንጀል ፈፃሚ አካላትና ስብስቦች የሚፈጽሙት ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት አገሪቷና

ሕዝቧ ከ27 ዓመታት የህወሓት/ኢ.ህአዴግ ኢ-ዴሞክራሲያዊ፣ አሰቃቂና ጨቋኝ አገዛዝ ወጥተው ብሩህ ተስፋ አይተው ወደፊት ለመጓዝ በሚያስቡበት ወቅት መሆኑ ደግሞ ወንጀሉን እጅግ ያከብደዋል። ስለሆነም፦ ኢ.ሕ.አ.ፓ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሃሳቦች ያቀርባል።

1) መንግሥት በሕግ የሚጠበቅበትን ሰላምና መረጋጋትን የመፍጠር ግዴታውን በአፋጣኝ መወጣት ለነገ የማይባል ተግባር በመሆኑ አስቸኳይ እርምጃ እንዲወስድ፣ ኢ.ሕ.አ.ፓም የሚቻለውን ሁሉ በማድረግ ድጋፉን ይሰጣል።
2) የመንግሥት አንዱና ዋነኛ ተግባር የኢትዮጵያን ሕዝብ በሀገሩ ውስጥ በሰላም እንዲኖር ማድረግና ከወንጀለኞች መከላከል በመሆኑ፣ ወንጀል ከመፈጸሙ በፊት ቅድመ-ጥንቃቄ ማድረግ፣ ወንጀል ከተፈጸመ በኋላ ደግሞ ወንጀለኞችን ለፍርድ ማቅረብ ይገባዋል። ይህ ሳይሆን እያንዳንዱ ዜጋ ፍትኅን በራሱ ለማስፈጸም ከሞከረ አገራችን እጅግ አደገኛ ወደሆነ የእርስ በርስ ጦርነት አቅጣጫ ልትገባ እንደምትችል መረዳት ያስፈልጋል። ስለሆነም መንግሥት የህግ የበላይነትን በአስቸኳይ ማስከበር አለበት።
3) የመንግሥት የለውጥ አመራር በህወሓት የአፈናና ኢ-ዴሞክራሲያዊ መዋቅር ላይ ተመሥርቶ ያለመውን ከግብ ለማድረስ እንደማይችል ተገንዝቦ ቁልፍ የሆኑ ቦታዎች ላይ ተቀምጠው ሕዝቡን የሚያምሱትን ጎጠኛ ፖለቲከኞችን ከሥልጣናቸው ዘወር ማድረግ ይገባዋል። ይህ ደግሞ የተጀመረውን የለውጥ ሂደት ለማስቀጠልና እንዳይቀለበስ ለማድረግ ወሳኝ እርምጃ ነው።
4) የመገናኛ ብዙሀን ለሀገሪቱ አንድነትና የሕዝብ ሰላም እንዲጠበቅ በሃቅና በማስረጃ ላይ የተመሠረተ ሥራ መሥራት ይገባቸዋል። ይህንንም በትክክል መፈጸማቸውን መንግሥት መከታተል ይኖርበታል።
5) በሕዝብ መካከል ግጭት እንዳይፈጠር ሰፊና ተከታታይ ሕዝባዊ ስብሰባዎች እየተደረጉ እያንዳንዱ ዜጋ ስለሰላም የበኩሉን እንዲያበረክት ማድረግ ያስፈልጋል።
6) በጎሣ/በቋንቋ ላይ የተመሠረተው ፌዴራሊዝም የችግሮቹ ሁሉ መንስዔ በመሆኑ ከጥላቻና ከመከፋፈል ሂደት መላቀቅ የሚቻለው በሥራ ላይ ያለው ሕገ መንግሥት ሲሻሻል ስለሆነ የፓለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማኅበራት፣ የመገናኛ ብዙሃን በአጠቃላይ የሀገሪቱ ዜጎች ሕገ- መንግሥቱን እንዲያሻሽሉ ሂደቱን ማስጀመር ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሉዓላዊነትና የሀገሪቱ የግዛት አንድነት በትግሉ ይከበራል!